# የቴሌኮሚኒኬሽን ህጋዊ ታሪፍ መመሪያ ማብራሪያ

[School]
[Course title]

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን አገልግሎትን በተመለከተ የፖለሲ ለውጥ እንዳደረገች ይታወቃል። ከዚህ በፊት በመንግስት እጅ ብቻ የነበረው የቴሌኮም ኢንዱስትሪ ለሃገር ውስጥ እና ለውጪ ባለሃብቶች ክፍት እንዲሆን ተደርጓል። ይህን ተከትሎም ከአንድ በላይ የሆኑ የቴሌኮም ኦፕሬተሮች ወደ ስራ ይገባሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን እነዚህ ኦፕሬተሮች ለአገልግሎታቸው የሚያስከፈሉት ዋጋ ወጪን መሰረት ያደረገ እና የቴከኖሎጂውን ተደራሽነት ያገናዘበ መሆን አለበት።

ለዚህም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የታሪፍ አወሳሰን እና አተገባበር ላይ ጠንካራ የቁጥጥር ስራን መስራት የሚጠበቅበት ሲሆን ለዚህ አጋዥ የሆኑ ድንጋጌዎች ማውጣት እና የአሰራር ስርሃት መዘርጋት አለበት። ይህን መሰረት በማድረግ የቴሌኮምኒኬሽን ህጋዊ ታሪፍ መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን ይህም በዘርፉ ውጤታማ ስራን መስራት ያስችላል ተብሎ ይታመናል።

## 2. የመመሪያው የሕግ መሰረት

የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 አንቀጽ 6(6) ፥ 45(5) ፥ 46(1) እና 54(2) መሰረት የህጋዊ ታሪፍ መመሪያ ማውጣት እንደሚችል ተመልክቷል። በአዋጁ አንቀጽ 46(1) ላይ ባለስልጣኑ የማንኛውንም ፈቃድ ያለው የቴሌኮመኒኬሽን ኦፕሬተር ታሪፍ ለመገምገም፥ ለመቆጣጠር እና ታሪፉ ሕጋዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የታሪፍ ዝግጅት መመሪያ የማወጣት ስልጣን እንዳለው ተመልክቷል። ከዚህም በተጨማሪም በአዋጁ አንቀጽ 45(5) ላይ ባለስልጣኑ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው በታመነ የቴሌኮመኒኬሽዕን ኦፕሬተር የቀረበውን ታሪፍ ሕጋዊነት የሚወስንበትን ደረጃ እና የአሰራር ስርሃት እንደሚያዘጋጅ ይናገራል። ከዚህ ባሻገርም ባለስልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 54 (2) መሠረት አዋጁን እና አዋጁን መሠረት አድርገው የወጡ ደንቦችን የማስፈጸሚያ መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን የተሰጠው ሲሆን እነዚህን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## 3. የመመሪያው ዓላማ

ይህ መመሪያ የተለያዩ አላማዎችን ከግብ ለማድረስ የተዘጋጅ ሲሆን በዚህ ክፍል ዋና ዋና ሊባሉ የሚችሉ የመመሪያውን አላማዎች ተመልከተዋል፤-

- የቴሌኮመኒኬሽን ኦፕሬተሮች ታሪፍን ህጋዊነት ለመገምገም፥ ታሪፍ ለመጣል ወይም ታሪፎችን ለመከለስ ተግባር ላይ የሚያውላቸው ህጎች እና የአሰራር ስርሃቶች ላይ ግልጽነትን መፍጠር፥
- የቴሌኮመኒኬሽን ኦፕሬተሮች ታሪፍ መቀየር ወይም አዲስ ታሪፍ ማስቀመጥ ሲፈልጉ ሊከተሏቸው የሚገቡ ህጎች ላይ እና የአሰራር ስርሃቶች ላይ ግልጽነት መፍጠር፥
- የቴሌኮምኒኬሽን ኦፕሬተሮች ለአገልግሎቶቻቸው ህጋዊ ያልሆኑ እና ወጪን መሰረት ያላደረገ ታሪፎችን ከተጠቃሚው እንዳይጠይቁ ክልከላን መጣል፤

## 4. የመመሪያው የዝግጅት ሂደት

የመመሪያው ዝግጅት ከአንድ አመት በላይ የወሰደ እና በርካታ ሂደቶችም ያለፈ ሲሆን ረቂቅ ህጉ ተጠናቅቆ እስከቀረበበት ድረስ የተከናወኑ አበይት ተግባራት ወይም ሂደቶች በሚከተለው መልኩ ተጠቃልሏል።

- **ጥናት ማካሄድ፡-** እስካሁን ድረስ ህጋዊ የቴሌኮመኒኬሽን አገልግሎት ታሪፍን የተመለከቱ ህጎች እና ልምዶች አንደ ሃገር አልነበረንም። በመሆኑም ይህን መመሪያ ለማዘጋጀት ዘርፉን መሰረት ያደረገ ጥናቶች ማካሄድና በጥልቀት መረዳት የሚጠይቅ ነው። ይህንን ለማሳካት የሃገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ፥ በዘርፉ የዳበረ ልምድ ያላቸው የሃገራት ተሞክሮ እና የቴክኖሎጂ እድገት በተመለከተ ጥናት ተደርጎል። በዚህ ጥናት አማካኝነት በመመሪያ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ድንጋጌዎች እና ዋና ዋና ቁም ነገሮች ተለይቷል።
- **ለረቂቅ ህጉ ዝግጅት ግብአት የሚሆኑ ሞዴል ህጎችና ተሞክሮዎች መምረጥ፡-** የቴሌኮም ዘርፍ ላይ አለም-አቀፍ ተቋማት ተሳታፊ በመሆናቸው ዘርፉን የሚያስተዳድረው ህግም አለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ መዘጋጀት አለበት። ስለሆነም የህጉ ይዘት አለም አቀፍ ደረጃው የጠበቀ ይሆን ዘንድ ከሃገሪቱ ማህበራዊ፥ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች አንጻር ተቀራራቢ የሆኑ ሃገራት ህጎች በሞዴልነት በመምረጥ ልምዶች ተወስደዋል።
- **ባለድርሻ አካላትን ማወያየት፡-** ረቂቅ መመሪያውን ለማዳበር የሚከተሉት ሶስት የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተዋል፡-
    - የሃገር ውስጥ እንዲሁም አለማቀፍ የቴሌኮም ኦፕሬተሮችን፥ ከዘርፉ ጋር ግንኙነት ያላቸው የመንግስት እና የግል ባለደርሻ አካላትን፥ የሲቪክ ማህበረሰብን፥ ዘርፉ ላይ የሚሰሩ የህግ ባለሙያዎችን ፥ባለሃብቶችን ወዘተ ተሳታፊ ያደረገ የአንድ ወር የምክከር መድረክ ተዘጋጅቷል።

- ረቂቁን በባለስልጣኑ ዌብሳይት ላይ ለ20 ቀናት ለሕዝብ አሰተያየት ክፍት እንዲሆን ተደርጎ፤ ፍላጎቱ ካላቸው የሃገር ውስጥ እንዲሁም አለማቀፍ ተቋማት በቂ የሆነ ግባት ለመሰብሰብ ተችሏል።
- ባለድርሻ አካላት ያነሱት ነጥቦችን እና ባለስልጣኑ የሰጠውን ምላሽ በተመለከተ ሦስተኛ የምክክር መድረክ ተዘጋጅቷል። በዚህ መድረክ ላይ በተሳታፊዎች የተነሱ ነጥቦች ላይ ውይይት የተደረገ ሲሆን በመመሪያው ላይ ሊካተቱ የሚገቡ ተጨማሪ ግባቶች ተገኝተዋል።

## 5. በረቂቅ መመሪያው ላይ የተነሱ ነጥቦች እና የተወሰዱ እርምጃዎች

በረቂቅ መመሪያው ላይ የተለያዩ የሃገር ውስጥ እና የውጪ ሃገር ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ የሆኑ ሲሆን በመድረኩ ላይ የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተዋል። ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋና ናቸው።

- በአዋጁ የተሰጡ ስልጣኖች እንደተጠበቁ ሆነው በመግቢያ (preamble) ክፍል ላይ መመሪያውን ማውጣት ያስፈለገበት ዋና ምክንያቶች ተለይተው በአንድ ወይም ሁለት ፓራግራፍ ውስጥ እንዲካተት ቢደረግ፤
- ሕጋዊ ታሪፍ የሚለው የመመሪያው ርህስ ከሌላ የሃገሪቱ ህግ ጋር አብሮ ስለማይሄድ የቴሌኮመኒኬሽን ህጋዊ ታሪፍ በሚለው ቢተካ፤
- የክፍል አንድ ርዕስ ዝርዝሮቹን በማስወጣት ጠቅላላ በሚል እንዲስተካከል ቢደረግ፤
- በአዋጁ ውስጥ የተካተቱ በዚህም መመሪያ ላይ በድጋሚ አንዲካተቱ የተደረጉ ቃላቶች እንዲወጡ ቢደረግ። በአዋጁ ላይ የተሰጡ የቃላት ትርጓሜዎች መመሪያው ላይ ተፈጻሚ አንደሆኑ እስከተመለከቱ ድረስ መመሪያው ላይ መድገም አያስፈልግም፤
- በመመሪያው የውስጥ ክፍል ላይ ትርጓሜ የሚመሰሉ አንቀፃት ይገኛሉ። እነዚህ ድንጋጌዎች በትርጉም ክፍሉ ላይ ፍቺ ስለተሰጣቸው እዚህ መድገም አያስፈልግም።
- አንቀጽ 5 ላይ የባለስልጣኑ ሚና ተብሎ የተገለጸው በውስጡ ከያዘው የድንጋጌ ሐሳብ ጋር አይሄድም። ስለሆነም ሚና የሚለው ቃል ተግባር እና ሃላፊነት በሚለው ቢተካ፤
- ባለስልጣኑ የኦፕሬተሩን ማመልከቻ ተመልክቶ ምላሽ የሚሰጥበት ግዜ ግልጽ አይደለም። ባለስልጣኑ በተቀመጠው ግዜ ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ፤ ማመልከቻው ውድቅ እንደሆነ ይቆጠራል

የሚለው አባባል ተገቢ አይደለም። ከዚህም በሻገር የቀረበን ማመልከቻ ባለስልጣኑ ውድቅ ሲያደርግ ተገቢውን ምክንያት በጽሁፍ ማቅረብ እንዳለበት ቢያመለክት የተሻለ ነው፤

- ሕዳግ ጥበት ምን ማለት እንደሆነ ግልፅነት ለመፍጠር በትርጓሜ ክፍል እንዲካተት ቢደረግ፤
- ባለስልጣኑ በኦፕሬተሩ በኩል ለቀረብ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥበት ግዜን በተመለከተ የተነሳው አስተያየት አግባብነት ስላለው ተገቢው ማሻሻያ ተደርጓበታል፤
- መመሪያውን ማሻሻል በተመለከተ ክፍል ላይ መመሪያው በማንኛውም ወቅት እንደሚሻሻል ተደንግጓል። ይህ ግን የባለፍቃዶችን ጥቅም ስለሚጎዳ ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ የሚሆኑበትን ሁኔታ ቢፈጠር።

ከላይ የተመለከቱት እና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን ባለስልጣኑም የሃገሪቱን ጥቅም እና የቴክኖሎጂውን መስፋፋት የሚኖረውን ፋይዳ ግንዛቤ ውስጥ በመክትት የሚከተሉት ውሳኔዎች ተወስነዋል፡-

- የመመሪያው ርዕስ ላይ የተነሳው ጥያቄ አግባብነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል፤
- መግቢያው ላይ የተነሳው ጥያቄ አግባብነት ያለው በመሆኑ ማሻሻያ ተደርጓበታል።
- ክፍል አንድ አወቃቀር ላይ የተነሳው ሐሳብ ተገቢነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል፤
- ሕዳግ ጥበት የሚለው ቃል በዚህ መመሪያ ፍቺ ይሰጠው የሚለው ጥያቄ ተገቢነት ስላለው ትርጓሜ ተሰጥቷታል፤
- በአዋጁ ላይ የተመለከቱ ቃላቶች በመመሪያ ውስጥ በድጋሚ የተካተቱበት ሁኔታ ስላለ ተገቢው ማሻሻያ ይደረግበት የሚለው ሐሳብን በመቀበል ከፊል ማሻሻያ ተደርጓበታል።
- መመሪያውን ባለስልጣኑ በማንኛውም ወቅት እንደሚያሻሽለው የተመለከተው ንግግር የአገልግሎት ሰጪዎችን ፍላጎት ስለሚጎዳ ይሻሻል የሚለው ጥያቄ ተገቢነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል።

## 6. ለውይይት የተሰራጨው ረቂቅ መመሪያ እና የመጨረሻ ሆኖ የወጣው መመሪያ

- በመመሪያው መግቢያ ላይ ለመመሪያው መሰረት የተደረጉ ድንጋጌዎች ብቻ ናቸው የተካተቱት። ለመመሪያው መውጣት ምክንያት የሆኑ ነጥቦች አልተካተቱም የሚል አስተያት ከባለደርሻ አካላት በኩል ቀርቧል። ስለሆነም የመመሪያው መግቢያ የመመሪያውን አስፈላጊነት

አጉልቶ በሚያሳይ መልኩ በድጋሚ ይስተካካል የሚለው ሐሳቤ/ አስተያት ተገቢ በመሆኑ በዛ መልክ እንዲስተካከል ተደርጓል።

- ትርጉም ክፍል ላይ የተነሳው ነጥብ ተገቢነት ስላለው ከትርጉም ክፍል አወቃቀር ጋር በተያያዘ የተነሳው አስተያየት በከፊል እንዲሻሻል ተደርጓል።
- ክፍል አንድ የተዋቀረበት መንገድ የሃገሪቱን የህግ አወቃቀር የተከተለ አይደለም የሚለውን ጥያቄ በመቀበል በሃገሪቱ የተለመዱ የህግ አወቃቀር ተፈጻሚ እንዲሆን ተደርጎል፤
- በመድረክ ተሳታፊዎች ፍቺ የሚያስፈልጋቸው ቃላቶች ተለይተው የቀረቡ ሲሆን ለእነዚህ ቃላቶች ትርጓሜ ተሰጥቷቸዋል።
- ለውይይት በቀረበው ሰነድ ላይ "ታሪፍን በተመለከተ ለባለስልጣኑ የቀረበ ጥያቄ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልተሰጠው እንዳልጸደቀ ይቆጠራል" የሚለው ድንጋጌ ላይ የተነሳውን አስተያየት በመቀበል--"-በአስራ አምስት የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልተሰጠው፤ እንደጸደቀ ይቆጠራል በሚለው ተተክቷል"።
- በማስታወቂያ በተሰራጨው መመሪያ ላይ ባለስልጣኑ መመሪያውን በማንኛውም ወቅት እንደሚያሻሽለው ተመልክቷ የነበረ ሲሆን በመጨረሻ ረቂቅ ላይ ግን ባለስልጣኑ መመሪያውን ሲያሻሽል ከባለድርሻ አካላት ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ማድረግ እንደሚኖርበት ተመልክቷል። ይህ የተደረገበት ዋና ምክንያት ባለስልጣኑ በየወቅቱ ባለድርሻ አካላትን ሳያሳትፍ ማሻሻያ የሚያደርግ ከሆነ የአገልግሎት ሰጪዎችን ፍላጎት/ጥቅም ይጎዳል ከሚል ሐሳቤ የተነሳ ሲሆን ይህም ከባለድርሻ አካላትም በኩል በስፋት ሲንጸባረቅ ነበር። ጥያቄው የአዋጁን መንፈስ ያገናዘበ እና ተገቢ በመሆኑ እንዲስተካከል ተደርጓል።